# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

*ተዛማጅ ምንጮች፡-* ABA-RB, ABA-RC, COC-RA, EBC-RA, ECA, ECM, ECM-RA, EEA, EEA-RA, JNA-RB, KGA-RA

*ሀላፊነት ያለባቸው ቢሮዎች፡-* የስራ ሂደት ዋና ሀላፊ፣ የት/ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ዋና ሀላፊ/Chief Operating Officer, Chief of School Support and Well-being

## የመኪና ማቆሚያ/ፓርኪንግ/ መገልገያዎች እና የተማሪዎች መኪና ማሽከርከር

I. **ዓላማ**

ተማሪዎች ለሚያሽከረክሯቸው መኪናዎች በት/ቤቶች የሚገኙትን የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች አቅርቦትን በሚመለከት በአካባቢ ት/ቤቶች ደንቦች እንዲዘጋጁ መመሪያ ለመስጠት፡-

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ይዞታ ስር የሚገኙ ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጥቅም ላይ እንዲውሉ በኮንትራት የተያዙ ቦታዎችን፣ ከዚህ በኋላ "MCPS የመኪና ማቆሚያ መገልገያዎች" ተብሎ ይጠራል፣ ይህንን በሚመለከት የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ እና ከመኪና ማቆሚያ መገልገያዎች መኪና ማስነሳትን/towing በሚመለከት የሜሪላንድ ህጎችን ለመተግበር የአሰራር ቅደም ተከተሎችን ለማስቀመጥ

II. **ዳራ**

በቦርድ ፖሊሲ ECA መሠረት፣ በዘላቂነት ተስማሚ በሆነ መልኩ፣ ሰራተኞች እና ተማሪዎች ወደ ት/ቤት መኪና እየነዱ መምጣት በአካባቢያዊ የአየር ንብረት ብክለት ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው እንዲያስቡበት ያበረታታል፥ እና በእግር ተጉዘው ወደ ት/ቤት ለመምጣት ርቀው ለሚኖሩ ተማሪዎች እና ርቀቱ ግምት ውስጥ ሳይገባ በእግር የመጓዝ ሁኔታቸው ለአደጋ የሚያጋልጣቸው ተማሪዎች፥ እና ተማሪ ለግላዊ የትምህርት ፕሮግራሙ የተለየ መጓጓዥ/ትራንስፖርት የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር ለሁሉም ተማሪዎች MCPS የትምህርት ቤት አውቶብስ ትራንስፖርት ያቀርባል።

III. **MCPS የመኪና ማቆሚያ ቦታ ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልግ ሲሆን ፈቃድ የሌላቸውን ተሽከርካሪዎች በመኪና ጎትቶ የማስነሳት እርምጃ ይወሰዳል።**

A. MCPS የመኪና ማቆሚያ መገልገያዎች የተዘጋጁት ለ MCPS ሰራተኞች፣ ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው፣ እና የ MCPS ስራ በሚያከናውኑበት ወቅት የ MCPS ትምህርት ቤቶች/መገልገያዎችን ለመጠቀም እንዲችሉ ፈቃድ ለተሰጣቸው ጎብኚዎች ነው።

B. የፋይናንስ ቢሮ (OOF) ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች የመኪና ማቆሚያ ቦታ ፈቃድ በሚመለከት አመታዊ መመሪያ የመስጠት ሃላፊነት አለበት።

C. ስርዓት-አቀፍ የደህንነት እና ድንገተኛ/አስቸኳይ ጊዜ አስተዳደር ክፍል (DSSEM) ርእሰመምህር ወይም የመገልገያው አስተዳደር ጥያቄ ሲያቀርብ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመኪና ማቆሚያ ቦታ/ፋሲሊቲ/መገልገያ፣ መኪና ተጎትቶ የሚወገድበትን አሰራር ሊተገበር ይችላል።

1. DSSEM የሜሪላንድ ህግን በማክበር፣ ተግባራዊ የሆነ መኪና በተጎታች የሚወገድበትን አሰራር

ማስታወቂያ በሚታይ ቦታ ላይ ማስቀመጥን ያዛል፣ መኪና በተጎታች የሚወገድበት አሰራር ቅደም ተከተሎችን ለመተግበር ከዲስትሪክቱ የስራ ሀላፊ ቢሮ እና ከጀነራል ካውንስል ቢሮ ጋር ይማከራል። መኪና ጎትተው ወይም ጭነው የሚያስወግዱ ኩባንያዎች/Tow truck companies የሜሪላንድ ህግን አክብረው የመስራት ሀላፊነት አለባቸው፣ ይሄውም ከ MCPS የመኪና ማቆሚያ መገልገያ ቦታ 15 ማይል በላይ ርቆ ወደሚገኝ ቦታ የተጫኑ/የሚጎተት-መኪና ማከማቻ ቦታ ላይ ጎትቶ መውሰድን የሚገድብ ነው።

2. መኪና ተጎትቶ መወገድ ያለበት ሁኔታ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ፣ በርእሰመምህር/የመገልገያ ቦታ አስተዳዳሪ ጥያቄ መሰረት መኪና ተጎትቶ እንዲወገድ የማመቻቸት ሀላፊነት ያለበት DSSEM ነው። ትኩረት የሚያሻቸውን አሳሳቢ ወይም አስቸኳይ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት መኪና ተጎትቶ እንዲወገድ (tow) የሚደረገው በርእሰመምህር/የመገልገያ ቦታ አስተዳዳሪ ውሳኔ ነው።

3. DSSEM ሳይፈቀድ ርእሰመምህራን/የመገልገያ ቦታ አስተዳዳሪዎች በግላቸው መኪና ተጎትቶ እንዲወገድ/ቶው ማስደረግ አይችሉም።

4. DSSEM የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመኪና ማቆሚያ መገልገያዎች እንደ አስፈላጊነቱ ለሰራተኞች መጠቀሚያ እንዲሆኑ የተሸከርካሪ መለያዎችን ወይም ሌሎች ምልክቶችን ይሰጣል።

D. መኪና ለማቆም/ፓርክ ማድረግ የተከለከሉ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መኪና ማቆሚያ መገልገያዎች በዚህ ብቻ ባይገደብም የሚያካትተው –

1. ከ 12:00 a.m. እስከ 5:00 a.m. መካከል ባሉ ሰአታት[1]፤

2. በእሳት አደጋ መከላከያ መተላለፊያ ጎዳናዎች ላይ፤

3. አካል ጉዳተኝነቶች ላለባቸው ግለሰቦች የተመደቡ ቦታዎች፣ ከስቴት-የተሰጠ የአካል ጉዳተኝነት ምልክት ሳያስቀምጡ ወይም የዚህ አይነት የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን መጠቀም የሚፈቅዱ የፈቃድ ምልክቶችን ሳያስቀምጡ፤

4. የመኪና መንገድ መንገዶችን ወይም ባዶ የሆኑ ቦታዎችን በሚዘጋ ሁኔታ ውስጥ፣

5. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ይዞታን ለቀው እንዲወጡ ሲጠየቁ እምቢ በሚሉበት ወቅት፣ MCPS ደንብ COC-RA፣ MCPS ንብረት ላይ ጥሶ መግባት ወይም አውቆ መበጥበጥ ድንጋጌ መሰረት፤ ወይም

6. ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስራ ጋር ወይም ከማህበረሰብ መገልገያዎችን የመጠቀም ሁኔታ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የንግድ ድርጅት ወይም የነዋሪዎች አጠቃቀም ጋር የሚዛመዱ ጉዳዮች MCPS ደንብ KGA-RA፣ በፐብሊክ ስኩልስ የማህበረሰብ አጠቃቀም ላይ በተቀመጠው መሰረት፥

## IV. *የተማሪዎች መኪና ማቆሚያ*

MCPS የራሳቸውን መጓጓዣ መጠቀም ለሚጠበቅባቸው ተማሪዎች የተወሰነ ቁጥር የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን

[1] ከተጠቀሱት ሰዓታት በኋላ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን መጠቀም አስፈላጊ የሚያደርጉ የት/ቤት ዝግጅቶች፣ የአየር ሁኔታ ወይም ሌሎች ሁኔታዎች ሲኖሩ፣ ርእሰመምህር/የመገልገያ ቦታ አስተዳዳሪ መኪና ከማቆሚያ ቦታ እንዲነሣ/ቶው እንዲደረግ ጥያቄ ማቅረብና ውሳኔ መስጠት ይችላል።

መስጠት ይችላል።

A. እያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዳይሬክተር፣ በየአመቱ፣ ለተማሪዎች መጠቀሚያ የሚሆኑ በት/ቤት ቅጥር ግቢዎች ውስጥ የሚገኙ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን ቁጥር ይወስናሉ።

B. ለተማሪዎች የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ መብት ሳይሆን ተጨማሪ ጥቅም ነው።

C. ተማሪዎች የት/ቤት ይዞታ በሆኑ ቦታዎች ላይ ተሽከርካሪዎችን ስለመንዳት እና ማቆሚያ ቦታን መጠቀም ለሚመለከቱ ተያያዥ ህጎች እና የአካባቢ ት/ቤት መመሪያዎች በሙሉ ተገዢ ናቸው።

D. ለተማሪዎች የመኪና ማቆሚያ ቦታ ለማመቻቸት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ዳይሬክተር የአካባቢ ት/ቤት መመሪያ ለማዘጋጀት ከተማሪ ተወካዮች ጋር የመመካከር ሀላፊነት አለበት/ባት። የአካባቢ ት/ቤት መመሪያዎች የሚከተለውን ማካተት አለባቸው፡-

1. ወደ ት/ቤት መኪና እያሽከረከሩ መምጣት የአካባቢያዊ አየር ንብረት ብክለት ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ተማሪዎች እና ሰራተኞች እንዲያስቡ የሚያበረታቱ፣ እና ወደ ት/ቤት መኪና እየነዱ የሚመጡ ተማሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ ከአካባቢ ብክለት ጥበቃ አንፃር ዘላቂ የሆኑ የመጓጓዣ አማራጮችን የሚያስተዋውቁ ስልቶችን፥

2. ለተማሪ የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ ለመስጠት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተገቢ መሆን ያለባቸው –

   a) የአካል ጉዳተኝነት ላለባቸው ተማሪዎች፣

   b) በት/ቤት-የሚካሄዱ የስራ ፕሮግራሞች ላይ ለሚሳተፉ ተማሪዎች፣

   c) በትርፍ-ጊዜ በአካባቢ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ላይ ትምህርት ለሚከታተሉ ተማሪዎች፣

   d) በትርፍ-ጊዜ መርኃግብር የት/ቤት ክፍለ ጊዜያት ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች፣

   e) ከት/ቤት የትምህርት ሰአት-በኋላ በሚኖሩ ተግባራት ላይ ለሚሳተፉ ተማሪዎች፣ ወይም

   f) በዳይሬክተር እና/ወይም በተወካይ በሚወሰነው መሰረት መደበኛ ያልሆኑ የተማሪዎችን ፍላጎቶች ማሳካት ለሚፈልጉ ተማሪዎች።

3. የፈቃድ ጥያቄዎች እድሳት እና መስፈርቶች የጊዜ ገደቦች።

E. ዳይሬክተሮች ይሄንን ደንብ እና የአካባቢ ት/ቤት መመሪያዎችን፣ አሰራሮችን እና ከተማሪ የመኪና ማቆሚያ እና ከት/ቤት መኪና ማቆሚያ ፈቃድ ማመልከቻ ሂደት ጋር የሚገናኙ የጊዜ መርሃ ግብሮችን በሚመለከት ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች እና ለተማሪዎች ለማሳወቅ የተለያዩ የብዙሃን መገናኛ ስልቶችን ይጠቀማሉ።

F. የተማሪ መኪና ማቆሚያ በሚኖርበት ጊዜ ሁሉ የሚከተሉት የአሰራር ቅደም ተከተሎች መተግበር አለባቸው፡-

1. የተማሪ የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ የሚሰጠው MCPS ቅፅ 215-6፣ ለተማሪ የግል መኪና ለመጠቀም የወላጅ/የአሳዳጊ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ ከተሞላ እና ከተፈቀደ በኋላ ብቻ ነው። ት/ቤቶች ይሄንን መረጃ በኤሌክትሮኒክስ መሰብሰብ ይችላሉ፣ ነገር ግን የወረቀት ማመልከቻ

አሠራርም በተጨማሪ ማቅረብ አለባቸው።

2. ተማሪ በቅፅ 215-6 ተለይቶ ከተቀመጠው ውጪ ሌላ የቤተሰብ መኪናን መጠቀም ከፈለገ/ች፣ በት/ቤት ይዞታ ቦታዎች ላይ ለማቆም ተማሪው/ዋ መኪናውን በት/ቤት ቢሮ ማስመዝገብ አለበት/ባት።

3. የት/ቤት መኪና ማቆሚያ መገልገያዎችን ለመጠቀም ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች የመኪና መለያ ምልክቶች የሚሰጡት ከ OOF ት/ቤት እና ከፋይናንስ ስራዎች ቡድን ነው።

4. ለተማሪዎች የመኪና ማቆሚያ ያለው እያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተመላሽ የማይሆን ክፍያ ተማሪዎችን ሊያስከፍል ይችላል፣ ይሄም በቦርድ ውሳኔ እና ቅፅ 215-6 ላይ በተቀመጠው መሰረት ነው።

    a) ከተማሪ የመኪና ማቆሚያ የሚገኝ ገቢ መከናወን ያለበት ራሱን-የቻለ "Independent Activity Fund (IAF)" አማካይነት ነው። ገቢው መያዝ ያለበት ብቻውን IAF አካውንቲንግ ስርዓት ውስጥ ነው፥ እና በየዓመቱ የአመት-መጨረሻ የአትሌቲክ የገንዘብ ሪፖርት፣ እና በሌላ ሪፖርቶች ላይ እንደ አስፈላጊነቱ መካተት አለበት።

    b) ለእያንዳንዱ ት/ቤት ለአትሌቲክስ የተመደበ የስራ ማስኬጃ በጀት በስርዓት-አቀፍ የአትሌቲክስ ዳይሬክተር አማካይነት በከፊል የሚሟላው ከማንኛውም የተማሪዎች መኪና ማቆሚያ ክፍያዎች ከሚሰበሰብ ገቢ ወይም በቦርድ በሚወሰነው መሰረት ነው።

G. ባልተፈቀደ የተማሪ መኪና ማቆም የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጊዜያዊ ፈቃድ፣ የአካባቢ የመኪና ማቆሚያ መመሪያዎች ውጪ፣ ወይም ከላይ የተጠቀሰውን ሰክሽን III.C በመጣስ የመኪና ማቆም ላይ የሚወሰዱ የስነ-ምግባር እርምጃዎች፣ MCPS የተማሪ ስነ-ምግባር ህግ፣ እና ከሚከተለው ጋር ተስማሚ መሆን አለባቸው፡-

1. ይሄንን ደንብ የሚጥስ ተማሪ የመኪና ማቆሚያ ህጎችን በመጣስ ደረጃው እየጨመረ የሚሄድ የማስጠንቀቂያ እርምጃ ይወስዳል/ትወስዳለች። እነዚህ ደረጃቸው እየጨመረ የሚሄዱ ማስጠንቀቂያዎች፣ በዚህ ብቻ ባይወሰኑም የሚያካትቱት፡- የፅሁፍ ማስጠንቀቂያዎችን ወይም የሚለጠፉ የጥሰት ስቲከሮችን፣ ወይም ለቀን የመኪና ማቆሚያ ክፍያ ግዴታዎችን ሊሆን ይችላል።

2. የገንዘብ ችግር በሚኖርባቸው ሁኔታዎች ውስጥ፣ ተማሪው/ዋ ከገንዘብ ግዴታ ውጪ በአንዳንድ ተገቢ በሆኑ አማራጭ መንገዶች ት/ቤቱን የሚከሱበት እድል ይሰጣቸዋል፣ ይሄውም ዳይሬክተር በሚወሥነው መሰረት እና MCPS ደንብ JNA-RB፣ ከተማሪዎች መሰብሰብ ያለባቸው የገንዘብ ግዴታዎች ጋር በሚስማማ መንገድ ነው።

3. ደረጃው እየጨመረ የሚሄድ ማስጠንቀቂያዎች በኋላ፣ የተማሪ መኪና ቶው ሊደረግ/ተንትቶ ከቦታው ሊወገድ ይችላል። መኪናን ቶው ማድረግ ከላይ ከተጠቀሰው ሰክሽን III.B ጋር ተስማሚ መሆን አለበት።

**ተዛማጅ ማስረጃዎች፡-** አባሪ የሜሪላንድ ህግ፣ የመጓጓዣ/ትራንስፖርት አንቀፅ፣ ሰክሽን 21-10A-02፣ 03፣ እና 06።

**የዚህ ደንብ ታሪክ፡-** የቀድሞ ደንብ ቁጥር 215-3፣ ጃንዋሪ 21፣ 1980፤ ተሻሽሏል፥ ሜይ 2፣ 1988፤ ተሻሽሏል፥ ሴፕቴምበር 8፣ 1992፤ ተሻሽሏል፥ ሜይ 27፣ 1997፤ ተሻሽሏል፥ ጃንዋሪ 14፣ 2009፤ ተሻሽሏል፥ ሜይ 15፣ 2014፤ ተሻሽሏል ፌብሩዋሪ 21፣ 2023 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org